የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ ህዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

12th Year No. 6
ADDIS ABABA 17th November, 2005

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፮/፲፱፻፺፰ ዓ.ም

ለአዘዞ መተማ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ለማግኘት ከሳውዲ የልማት ፈንድ ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ … ገጽ ፫ሺ፫፻፲፫

CONTENTS

Proclamation No. 476/2005

Saudi Fund for Development Loan Agreement for Financing Azezo-Metema Road Project Ratification Proclamation.......... Page 3313

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፮/፲፱፻፺፰

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በሳውዲ የልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለአዘዞ-መተማ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፸ሚሊዮን፭፻ሺህ የሳውዲ ሪያል /ሰባ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ የሳውዲ ሪያል/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በሳውዲ የልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ሜይ ፲፰ ቀን ፪ሺ፭ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፰ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለአዘዞ-መተማ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ለማግኘት ከሳውዲ የልማት ፈንድ ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፮/፲፱፻፺፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION NO. 476/2005.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE SAUDI FUND FOR DEVELOPMENT

**WHEREAS,** a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Saudi Fund For Development stipulating that the Saudi Fund for Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount seventy million five hundred thousand (70,500,000) Saudi Riyals for financing the Azezo-Metema Road Project,

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 18th day of October, 2005;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows;

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Saudi Fund for Development Loan Agreement for Financing Azezo-Metema Road Project Ratification Proclamation No.476/2005."

ያንዱ ዋጋ 2.30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በሳውዲ የልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ሜይ ፲፰ ቀን ፪ሺ፭ የተፈረመው የብድር ስምምነት ፀድቋል፡፡

፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፸ሚሊዮን፭፻ሺ.ህ የሳውዲ ሪያል /ሰባ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ.ህ የሳውዲ ሪያል/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከህዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ህዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**2. Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement signed on the 18th day of May, 2005 between the Federal democratic Republic of Ethiopia and the Saudi Fund for Development is ratified;

**3. Power of the Minister of Finance and Economic Development**

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of seventy million five hundred thousand (70,500,000) Saudi Riyals in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. Effective Date**

The Proclamation shall enter into force on the 17th day of November, 2005.

**Done at Addis Ababa, this 17th day of November, 2005**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት